በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ

# የአሌ ቋንቋ ስርዐተ ድምፅ እና ስርዐተ ፅህፈት
# (Sound system and Orthography of Ale)

በሀረገወይን ከበደ እና ዮናስ በቀለ

2005 ዓ/ም

## የአሌ ቋንቋ ስርዐተ ድምፅ

በተለያየ ጊዜ አሌ ቋንቋ ላይ የስነልሳን ጥናት ያካሄዱ የስነ ልሳን ተመራማሪዎች በቋንቋው ውስጥ የሚገኙትን ድምፆች አስመልክቶ የተለያየ ቁጥር ሰጥተዋል። ለምሳሌ ብላክ(1976፡224) እና ገበረው(2003) አሌ 25 ተነባቢዎችና አምስት አናባቢዎች አሉት ሲሉ ፅፈዋል። ብላክ (1976: 224) የላንቃ ሰርናዊ [ɲ] እና የጉርአዊ (a pharyngeal fricative) [ħ] ድምፆቻ አሉ ሲል እነዚህ ድምፆች በሀረገወይን(2003፡42-56)ጥናት ውስጥ አልተካተቱም። በዚህ ጥናት የተገኙት 26 ተናባቢዎች እና 5 አናባቢዎች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ገበረው (voiced implosives) / ɓ/,/ ɗ/እና /ɠ/ ,ጉርአዊ (the voiceless pharyngeal)/ħ/ እንዲሁም እንጥላዊ (the voiceless uvular) /χ/ ድምፆችን በጥናቱ ግኝት ውስጥ አላካተተም።

ሮናልድ ሆስች ለዱላይ ቋንቋዎች ስብስብ የስርዐተ ፅህፈት ሀሳብ ባቀረበበት ጥናቱ ውስጥ 29 ተነባቢዎችንና 5 አናባቢዎችን ከሌሎች የጉርአዊነት (pharyngealized) አናባቢዎቻቸው ጋር እናገኛለን።

ከላይ የተመለከቱትን በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የጥናት ውጤቶችን ከመረመርንና አዲስ ከተሰበሰበው የቋንቋው መረጃ ጋር ካነፃፀርናቸው በኋላ በአሌ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙት ድምፆች 32 ተናባቢዎች እና 5 አናባቢዎች ናቸው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰናል። በተጨማሪም የአናባቢዎች መርዘም ወይም ማጠር እና የተናባቢዎች መጥበቅ ወይም መላላት በቃላት መካከል የትርጉም ልዩነት የሚያመጣ መሆኑን ከዚህ ጥናት ውጤት መገንዘብ ችለናል።

## በአሌ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ተነባቢ ድምፆች(Consonant Phonemes)

| | Bilabials<br>ከንፈራዊ | Labiodentals<br>ከንፈር ወስናዊ | Alveolars<br>ድዳዊ | Palatals<br>ላንቃዊ | Velars<br>ትናጋዊ | Uvulars<br>እንጥላዊ | Pharyngeals<br>ጉርአዊ | Glottals<br>ማንቁርታዊ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Plosives/እግድ/<br>Vd /ነዛሪ/<br>Vl /ኢነዛሪ/<br>Implosives /ውስጠ ፈንጅ/<br>Ejective /ፈንጂ/ | b<br>p<br>ɓ | | d<br>t<br>ɗ<br>ƭ | tʃ’ | g<br>k<br>ɠ<br>ƙ | ʛ | | ʔ |
| Fricatives /ሹልክልክ/<br>Ejective /ፈንጂ/ | | f | s z<br>s’ | ʃ | x | X | ħ ʕ | h |
| Affricatives<br>/ፍትግ/ | | | | tʃ | | | | |
| Nasals /ሰርናዊ/ | m | | n | ɲ | | | | |
| Lateral /ጎናዊ/ | | | l | | | | | |
| Flap /ላሽ/ | | | r | | | | | |
| Glides<br>/ከፊል አናባቢ/ | w | | | j | | | | |

**የእያንዳንዱን የአሌ ተነባቢ ድምፅ ስርጭትን ለማሳየት የሚከተሉት ቃላት በምሳሌነት ቀርበዋል።**

**/p/**

**piʔ:at:e** ልጅ ፍየል **por tʃo** ገብስ **irpante** መንጋ **gaspo** ስንዴ **tap:i** ስድስት

/b/

nabse ህይወት ʕarabgo ዝሆን tibo ተበተበ ħat'umbe መጥረጊያ

/d/

dilango ቂጣ adungo ጡት ande ውሀ

/ɓ/

ɓati ለካ iɓːe ፍሬ saɓi አቦካ ɓeɠi ገደላቸው tuɓa ውቀጡ tuɓ ውቀጥ!

/m/

muʃːo ቁርስ imːaje ቀበሩ orħami ተዋጋ tuːma ነጭ ሽንኩርት ħaːm ንቀል!

/w/

wale ቆንጨራ wawe ምራቅ hawle መቃብር kar:awo ፌንጣ taw:o እባብ !

/f/

foħo ሸለቆ piːfe ምሳ tafo ጭን/ታፋ ʔafte መኝታ saffa ዳህ !

/t/

tiʃe እሸት ɗoti ወጋ salete አዋጅ መንገር qayt:o ዓርብ sit ጥለፍ!

/ƭ/

ƭhile ክንድ t’eʔajo ትንሽ ፌንጣ jeħet’:i አስቀያሚ ħat'umbe መጥረጊያ • ut’ በጥስ(ጧ አድርገህ)!

/ɗ/

ɗipa ሙቶ ma:ɗe ጥሬ ɗu:t:ako ቁልቁለት iɗ:a ቀይ ɠut’aɗi ወሰነ

/k/

kolan ዘጠኝ kere መቀመጫ አይነት luk:alak:o አውራ ዶሮ lak:i ሁለት rak አንጠልጥላቸው!

/k’/

K’ark’ar:o እርዳታ hek’uri ራሱን ጣለ ik’aɠi ተፀዳዳ hok’aba እርጥብ hak’i ብጣ!

/g/

patango ጦባሳ tʃ'igno ፍቅር girtʃ'a የጆሮ ጉትቻ

/ɠ/

ɠubo ተራራ hoɠo ሽፍታ aɠa አለ oɠːa ɗːi ረገጠ liɠ ውጣ !

/n/

neħte ሴት( ለእንስሳ) awne ምሽት patango ጦባሳ man:e ቤት ɠun ላጭ!

/ɲ/

ɲari አስፈራራ ɲaɲa ቲማቲም maɲri ሪከስ ɲuƓe ጨቅላ

/l/

Le:me ቋቁ ቻ maltolakːo ራስ በራ luk:ale ዶሮ sutalo ተባይ fil አበጥር(ፀጉር) !

/r/

raʔ:o ቀይ ጉንዳን orːe ሽክላ ሰሪ karko እንጨት ature ድመት sorː ሩጥ !

/j/

hejho ምግብ isƓaje ቅማል imˑaji ቀበሪ paj በል !

/tʃ'/

tʃ'igno ፍቅር Ɠantʃari ፊቱን አኮማተረ kaːtʃ'e ጤፍ girtʃ'a የጆሮ ጉትቻ tʃ'eƓte ደም

/χ/

Xaf:i መጣ χasoɗi ደስ አለው ma χ:e እቃ χoχno ጉድጓድ a: χe ቅጠል

/x/

xai ተነሳ Ɠjxo ሰው

/z/

zija ጀግና izeh ሶስት

/ɠ/

ɠ u ɠ ጠምዝዝ ! soɓ or ɠ o ትል is ɠ aje ቅማል ɠ o ɠ e ቅርፊት saq ! እረድ!

/ʔ/

ɓoʔi ፈነዳ ʔeme በግ kerʔko ሌባ raʔ ተኩስ!

/s/

salaħ አራት soak:o ጠንቋይ hosibletuba ቀጥቃጭ ise እሷ las: ሽጥ!

/s'/

kas'o ፀጉር

/ʃ/

ʃap: ane ቋጠሮ kiʃno ብዛት ʃel:ate ከሀዲ/ ዘራፊ muʃ፡o ቁርስ χaʃ ጥረብ/ቅርፅ አውጣ!

/tʃ/

tʃele ካብ tʃaħan ሰባት hejhitʃo እንግዳ arabatʃe ጅብ

/ħ/

ħanɗurte እትብት tʃaħan ሰባት salaħ አራት

/ʕ/

ʕarabgo ዝሆን puk:ʕate ራስ karʕito ሆድ

/h/

hawle መቃብር huiɗ፡a ቀዩ tahan ሰባት hoɗam:a ታላቅ hermale የሜዳ አህያ

## አናባቢዎች (Vowels)

አሌ እንደአብዛኞቹ የኩሽ ቋንቋዎች  የሚከተሉት 5 አናባቢዎች አሉት።

## የአሌ የአናባቢ ድምፆች ስርዐት (Vowels system of Ale)

| | Front | Central | Back |
|---|---|---|---|
| Close | i [i] | | u [u], |
| Mid | e [e] | | o [o], |
| Open | | a [ɑ], | |

## የአሌ ስርዐተ ፅህፈት (The orthography)

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በተደረገው የስነ ድምፅ ፍተሻ መሰረት በአሌ ቋንቋ ውስጥ 30 ተነባቢ ድምፆችን መለየት ተችሏል። እነዘህ ተነባቢ ድምፆችን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን። በመጀመሪያው ክፍል ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ተነባቢዎች ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ንበት ያላቸውና በእንግሊዘኛው ፊደላት ምልክቶች ሊወከሉ የሚችሉ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ በአሌ ቋንቋ ውስጥ ብቻ የሚገኙና በእንግሊዘኛ ፊደላት ሊወከሉ የማይችሉ ድምፆች ናቸው።

ከእንግሊዘኛ ድምፆች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው የአሌ ድምፆች በሚከተለው መልክ በእንግሊዘኛ ፊደላት ተወክለው ቀርበዋል።

| Phonemes in IPA symbols | phones | Graphemes |
|---|---|---|
| /p/Voiceless bilabial plosive | [p] | <p> |
| /b/Voiced bilabial plosive | [b] | <b> |
| /d/ voiced alveolar plosive | [d] | <d> |

| | | |
|---|---|---|
| /m/Voiced bilabial nasal | [m] | <m> |
| /f/ Voiceless labio-dental fricative | [f] | <f> |
| /t/Voiceless alveolar plosive | [t] | <t> |
| /tʃ/Voiceless palatal plosive | [tʃ ] | <ch> |
| /s/Voiceless alveolar fricative | [s] | <s> |
| /z/ voiced alveolar fricative | [z] | <z> |
| /s’/voiceless alveolar ejective | [s’] | <s’> |
| /ʃ/Voiceless palatal fricative | [ʃ] | <sh> |
| /k/Voiceless velar plosive | [k] | <k> |
| /g/Voiced velar plosive | [g] | <g> |
| /n/Voiced alveolar nasal | [n] | <n> |
| /l/Voiced alveolar lateral | [l] | <l> |
| /r/Voiced alveolar trill | [r] | <r> |
| /w/Voiced bilabial glide | [w] | <w> |
| /j/Voiced palatal glide | [j] | <y> |
| /h/Voiceless glottal fricative | [h] | <h> |

በሁለተኛው ክፍል የሚመደቡት በአሌ ብቻ የሚገኙና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሌሉ ድምፆች አዳዲስ ወካይ ምልክቶች ያስፈልጋቸዋል። በመሆኑም እነዚህ ድምፆች በሚከተለው መንገድ የፊደል ውክልና እንዲኖራቸው ተደርጓል።

| **Phonemes in IPA symbols** | **Phones** | **Graphemes** |
|---|---|---|
| /t’ /Voiceless alveolar ejective | [t’] | <t’> |
| /k’ / Voiceless velar ejective | [k’] | <k’> |
| /tʃ' /Voiceless palatal affricate | [tʃ’] | <c’> |
| /ɲ/Voiced palatal nasal | [ɲ] | <ny> |

| | | |
|---|---|---|
| /ʔ/Voiced glottal plosive | [ʔ] | <ʔ> |
| /x/Voiceless velar fricative | [x] | <x> |
| /χ/Voiceless uvular fricative | [χ] | <hx> |
| / ħ/Voiceless pharyngeal fricative | [ħ] | < ħ > |
| /ʕ/ voiced pharyngeal fricative | [ʕ] | <ʕ> |
| /ɓ/Voiced bilabial implosive | [ɓ] | <bh> |
| /ɗ/Voiced alveolar implosive | [ɗ] | <dh> |
| /ɠ/Voiced velar implosive | [ɠ] | <q> |
| /ʛ/Voiced uvular implosive | [ʛ] | <qh> |

/h/ ኢ-ነዛሪ ማንቁርታዊ ሹልክልክ (the voiceless glottal fricative) እንደሌሎቹ ምልክቶች ሁሉ ራሱን ችሎ ኢ-ነዛሪ ማንቁርታዊ ሹልክልክ (voiceless glottal fricative) /h/ ን እንዲወክል ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ ከ /b/ /d/ /q/ ጋር ተጣምሮ ሲመጣ የውስጠ ፈንጅ (implosive) ባህርይን ፣ ከ /s/ ጋር ተጣምሮ ሲመጣ ደግሞ የላንቃዊ ሹልክልክ (palatal fricative) የሆነውን / ʃ/ ን፣ ከ /c/ ጋር ሲጣመር ፍትግ የሆነውን / tʃ /ን እንዲወክል እንዲሁም ከ /x/ በፊት ሲመጣ የ ኢ-ነዛሪ እንጥላዊ ሹልክልክ (Voiceless uvular fricative) / χ/ እንዲወክል ተደርጓል። በተመሳሳይ መንገድ /y/ ብቻውን ሲፃፍ የ/j/ ን ድምፅ፣ ከ/n/ ቀጥሎ ሲፃፍ ደግሞ [ɲ] ን እንዲወክል ተደርጓል። በእንግሊዘኛ ቋንቋ ውስጥ የማይገኙ ነገር ግን በአሌ የሚገኙ የፈንጂነት ባህርይ ያላቸው እንደ /ጭ/ ፣/ጥ/፣ /ቅ/ እና /ፅ/ ድምፆች በላቲኑ /c/፣ /t/፣ እና /k/ ከላይ በቀኝ በኩል የ/'/ ወይም ጭረት ምልክት እንዲኖራቸው በማድረግ c' t' k' s' ድምፆችን እንዲወክሉ ተደርገዋል።

**የሚከተሉት ምልክቶች የአሌ አናባቢዎችን ወክለው ተፅፈዋል።**

| Phonemes in IPA | Phones | Graphemes |
|---|---|---|
| /i/ | [i] | <i> |
| /e/ | [e] | <e> |
| /a/ | [a] | <a> |

| | | |
|---|---|---|
| /o/ | [o] | <o> |
| /u/ | [u] | <u> |

## የአናባቢዎች ርዝመትና የተነባቢዎች ጥብቀት፤

አሌ  5 አጫጭርና 5 ረዣዥም አናባቢዎች አሉት። አጫጭሮቹ አናባቢዎች እያንዳንዳቸው ረዝመው ሲነበቡ የትርጉም ልዩነት ያመጣሉ።

**ምሳሌ**

| | |
|---|---|
| **aʃi** | 'ሄደ' |
| **aʃii** | 'ይሂድ' |
| **fara** | 'እየሞተ ነው' |
| **faara** | 'ይሙት' |
| **gatʃ'e** | 'አለንጋ' |
| **gaatʃ'e** | 'ጤፍ' |

ከምሳሌዎቹ እንደምንረዳው የአንድ አናባቢ አጥሮ ወይም ረዝሞ መነበብ የትርጉም ለውጥ ያመጣል። ስለዚህ ረዝሞ የሚነበብ አናባቢ ሁለት ሆኖ በመፃፍ አጭር ሆኖ ከሚነበበው አምሳያው መለየቱን ማሳየት አስፈላጊ ሆኖአል።

በተመሳሳይ መንገድ ተናባቢዎቹም ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የትርጉም ለውጥ ያመጣሉ።

**ምሳሌ**

| | |
|---|---|
| **lale** | 'ሞልቃቃ (ልጅ) |
| **lalle** | 'ልብስ' |

ለአናባቢዎቹ እንደተጠቀምነው ሁሉ ጥብቀትን በተመለከተ አንድ ተነባቢ ድምፅ ጠብቆ በሚነብበት ቦታ ሁሉ በሚጠብቀው ድምፅ አናት ላይ ሁለት ነጥብ በማኖር ለምሳሌ (**laÏe**) ካልጠበቀው አምሳያው ተነባቢ የተለየ መሆኑን እናመለክታለን።

## ስርዐተ ነጥብ

የአሌ ቋንቋን ለመፃፍ የተመረጠው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፊደል(የላቲን ፊደል) በመሆኑ አዳዲስ ስርዐተ ነጥቦች ለመፍጠር መሞከር ተገቢ አይሆንም። ስለዚህ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ስርአተ ነጥቦችን እንዳሉ በመውሰድ ለአሌ ልንጠቀምባቸው እንችላለን።

ከእነዚህ ስርዐተ ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው።

1.የአረፍተ ነገር መግቻ(ማብቂያ) (period) . አንድ ዐረፍተ ነገር ፅፈን ስንጨርስ አረፍተ ነገሩ ያለቀ መሆኑን ለማሳየት መጨረሻው ላይ ይህንን(.) ነጥብ እናደርጋለን።

ምሳሌ- Gudisa pifesi ipifi.

ጉዲሳ ምሳ በላ።

2. ነጠላ ሰረዝ (comma) , ነጠላ ሰረዝ የሚያገለግለው በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ ተመሳሳይ ሀሳቦች ወይም ቃላት ሲዘረዘሩ በመሀላቸው ፋታ እየሰጠን ማነበብ እንዳለብን ለማሳየት ነው።

ምሳሌ፡- ምሳሌ- Gudisaba, Nigusieba, kuse kume karo menekolingito sa ashe.

ጉዲሳ፣ ንጉሴ፣ ኩሴ ና ኩሜ ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ።

3. ድርብ ሰረዝ (semi colon) ; በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ሀረጎችን ወይም አረፍተ ነገር አከል ረጃጅም ሀሳቦችን ለመለየት ስንፈልግ ይህንን ስርዐተ ነጥብ እንጠቀማለን።

ምሳሌ፡-ምሳሌ- Gudisa rafate xaʕi; minte shoħomu; mañe kolengitosa ashi.

ጉዲሳ ከመኝታው ተነሳ፤ ፊቱን ታጠበ፤ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ።

4. የጥያቄ ምልክት (question mark) ? ጥያቄ መጠየቅ በሚያስፈልገን ጊዜ በጥያቄው መጨረሻ ላይ ይህንን ምልክት እናደርጋለን።

**ምሳሌ**- ato pife apifañaji?

ምሳህን ትበላለህ?

5. ትዕምርተ ጥቅስ (quotation) “ ” የሌላ ሰው ንግግርን እንዳለ ወስደን ስናቀርብ ንግግሩን በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ እናስቀምጣለን።

ምሳሌ- Gudisa yela pajna “mañe kolingitosa ashinayi”?

ጉዲሳ “ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለህ” ብሎ ጠየቀው።

6. ቃለአጋኖ (exclamation)! በፅሁፋችን ውስጥ አንድን ነገር አድንቀን ወይም በአንድ ነገር በጣም መገረማችንን ለማሳየት ስንፈልግ በቃሉ ወይም በሀረጉ መጨረሻ ላይ የቃለአጋኖ ምልክት እናኖራለን።

ምሳሌ፣ inti ifarayi!

ሞተ እንዴ!

7. ቅንፍ (bracket) () ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ሀሳብ ወይም ቃል የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የገባ ቃልን ወይም ከዋናው ሀሳብ እኩል ጠቃሚ ያልሆነ ነገር ግን ከተነሳው ሀሳብ ጎን መግባት የሚገባው ቃል ወይም ሀረግ ስንፅፍ በቅንፍ እናስገባዋለን።

ምሳሌ፣

ጉዲሳ (የኩሴ ወንድም) አዲስ አበባ ሄደ።

8. ህዝባር (slash) / ዓመተ ምህረት ሲፃፍ ቀኑን፣ ወሩን እና ዓመተ ምህረቱን ለመለየት ወይም በመደበኛ የደብዳቤ ፅሁፎች ላይ የሚሰጡ የደብዳቤ ቁጥር፣ ቀን... የመሳሰሉትን ለያይቶ ለመፃፍ የህዝባር ምልክት ያገለግላል።

ምሳሌ፣ 22/09/2005

9. ጭረት ( - ) ድርብ ቃላትን ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ቃላት የተመሰረቱ ቃላትን ለመፃፍ እንዲሁም በአንድ መስመር ላይ ተጠናቆ ያልተፃፈ ቃል ወደሚቀጥለው መስመር መሻገሩን ለማሳየት እንጠቀምበታለን።

ምሳሌ፣ man̈e-kolingto

ትምህርት-ቤት

10. ወዘተ(...) ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን በሙሉ መዘርዘር በማንፈልግበት ወቅት የተወሰኑትን ብቻ ፅፈን ሌሎቹም በእዚሁ መልክ ይቀጥላሉ ለማለት የምንጠቀምበት ስርዓት ነጥብ ነው።

ምሳሌ፣ morin̈a sagumoba, shinangoba, mangoba…alas̈a

እዚህ ገበያ ማር፣ ቅቤ፣ እህል...ይሸጣል።

## ቀጥሎ ያለው አጠር ያለ ምንባብ ለሙከራ በ አሌ ቋንቋ የተጻፈ ነው።

kedhay kdhan̈ati papoton̈e   pana yayi ẗe kalo kawadho nati ileẗa aga. longoẗon̈a mango xusindhi gïẗa paħak̈o kodhamadhi ẗa xoʕatitay ki ẗehusindhi kïẗaẗe ïleħule dhabe kodḧamadhi. xusïẗay xaʕati ïleħule im̈alale kabani dhik̈atate sabite ħadhiqe piÿaẗetay ïla araramepa hantu dhel̈e salaħki hxafasi pis̈i nagayhotay ʕaketeage.

## <u>ትርጉም</u>

በድሮ  ዘመን አንድ ባልና ሚስት ገዋዳ ከተማ ላይ አብረው ይኖሩ ነበር። አንድ ወቅት በአካባቢያቸው በተፈጠረ ረብሻ ምክንያት አለመግባባት በመካከላቸው ተፈጠረ። በዚህ ምክንያት ሳይስማሙ ቀሩ። በመጨረሻ ላይ ግን በአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ጥረት ታርቀው አሁን አራት ልጆችን አድርሰው በሰላም እየኖሩ ይገኛሉ።

# የአሌ ፊደል ገበታ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| a | i | o | n | k |
| t | e | u | y | s |
| p | r | l | g | m |
| dh | h | qh | sh | x |
| d | b | q | hx | w |
| f | ħ | z | ʔ | c’ |
| bh | t’ | k’ | s’ | ch |
| ʕ | ny | | | |

የአሌ ቋንቋ ድምጾች ውክልና በላቲን
Orthographic Representation Of sounds of Ale in Latin script

IPA
<u>Symbol</u> <u>Graphemes</u>

b <b>

p <p>

ɓ <bh>

t <t>

| | |
|---|---|
| ɗ | <dh> |
| ƭ | < ƭ > |
| tʃ’ | < c’ > |
| g | <g> |
| k | <k> |
| ɠ | <q> |
| ƙ | <k’> |
| ʛ | <qh> |
| ʔ • | <ʔ> |
| f | <f> |
| s | <s> |
| s’ | <s’> |
| ʃ | <sh> |
| x | <x> |

| | |
|---|---|
| d | <d> |
| χ | <hx> |
| ħ | < ħ > |
| z | <z> |
| h | <h> |
| ʕ | <ʕ> |
| tʃ | <ch> |
| m | <m> |
| n | <n> |
| ɲ | <ny> |
| l | <l> |
| r | <r> |
| w | <w> |
| j | <y> |